

# የቡድን ሥራ (አገልግሎት)

# TEAMWORK

ዶክተር ፓስተር ተስፋ ወርቅነህ

የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Christians Fellowship Church
8526 Northern St. Houston, Tx 77071
T. (713)484-5530 F. (713)484-5526
www.ecfchouston.org

# 1. መግቢያ

« የቡድን ስራ» (teamork) የሚለው ቃል በቤተክርስቲያንና ከቤተክርስቲያን ውጭ ባሉ ሰዎች አበክሮ የሚነሳ ሀሳብ ነው። ሰዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው የጋራ ውጤት ለማምጣት በሚጥሩበት ስፍራ ሁሉ «የቡድን ሥራ» «የቡድን ተጫዋች» «የቡድን መንፈስ» የሚሉትን ቃል መስማት እንግዳ ነገር አይደለም።

የቡድን ስራ በቤተክርስቲያን፣ በስፖርት ማኅበር፣ በሥራ ዓለም (corporate world) በሌሎችም አያሌ ድርጅቶች ውስጥ የአሰራር መርሆ ሆኖ በተግባር ላይ ይውላል። ቡድናዊነትን ለማጠናከር የቡድን ጥረትንም ለማብዛት በየድርጀቶቹ በሃሳቡ ላይ ብዙ ስልጠናና ትምህርት ይሰጣል። በዚህ ሀሳብ ላይ ትምህርትና አስተያየት የሚሰጡ መጸሕፍትና መጣጥፎችም ቁጥር ብዙ ነው።

## 1.2. ትርጉም

በቤተክርስቲያንና ከቤተክርስቲያን ውጭ የቡድን ሥራ ምን እንደሆነ የሚሰጠው ትርጉም ብዙ የሚራራቅ አይደለም።



### 1.2.1. ከቤተክርስቲያን ውጭ የሚሰጠው ትርጉም

ሀ) ቡድን - ሰዎች (ከአንድ በላይ) በአንድ ላይ ሆነው በጋራ ሲሰሩ
ለ) ቡድን - አንድ ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት በአንድ ዓላማ በአንድነት የሚሰሩ የሰዎች ሰብስብ (እያንዳንዱ ለቡድኑ የሚያበረክተው የራሱ አስተዋጽዖ ስላለ ቡድን የኃይልና የችሎታዎች ግምጃ ቤት ነው ይባላል።)
ሐ) የቡድን ስራ - በቡድን ለመስራት የተስማሙና የተሰባሰቡ ሰዎች የየግል ጥረታቸውን በጋራ አስተባብረው ሲሰሩ።
መ) የቡድን ጥረት (team effort) እያንዳንዱ ሰው የጋራውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ።
ረ) የቡድን ተጫዋች - (team player) የራሱን የግል ዓላማ በቡድኑ ዓላማ ተክቶ ውጤት ለማግኘት ያልተቆጠበ ጥረት የሚያበረክት የቡድን አባል።

### 1.2.2 በቤተክርስቲያን አካባቢ የሚሰጠው ትርጉም

ሀ) ቡድን - ቁጥራቸው የተወሰኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በአንድ ላይ በመተባበርና በመስማማት ችሎታቸውንና ስጦታቸውን በመጠቀም አብረው ሲያገለግሉ።
ለ) የቡድን ስራ - በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለተመሰረተ ዓላማ ሰዎች ልምምዳቸውን፣ እውቀታቸውንና ስጦታቸውን በአንድ ላይ አድርገው ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት ሲያገለግሉ።

- የአምልኮ ቡድን
- የመዘምራን ቡድን (ጓድ)
- የምስክር ቡድን (ጓድ) ወዘተ።

« የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» 1ኛ ቆሮንቶስ 3፥8
ሊቪንግ ባይብል በተባለው የእንግሊዘኛ ትርጉም ( TLB )

*“ Apollos and I are working as a team, with the same aim, though each of us will be rewarded for his own hard work “*

ሐ) የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ
1ኛ ቆሮንቶስ 12፥12-26
« አካልም ... »

### 1.2.3 ማጠቃለያ

ስለቡድን ስራ የሚሰጡት ትርጉሞች ሁሉ የሚከተሉትን አራት ባህርያት የሚያካትቱ ሊሆን ይገባል።

ሀ) ሁለት ወይም የበለጠ ሰው መኖር አለበት።
ለ) የጋራ የሆነ ዓላማና ግብ መኖር አለበት።
ሐ) የአንዱ ስራ በሌላው ስራ ላይ መመካት አለበት።
(task inter-dependence)
መ) ፍላጐታቸው የጋራ የሆነ ተመሳሳይ ውጤት ማምጣት መሆን አለበት።

## 2. የቡድን ሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት



### 2.1. የሥላሴ ምሳሌነት

የቡድን ሥራ በቅርብ የተገኘ አዲስ ነገር አይደለም። ለቡድን ሥራ ምሳሌ የሚሆነን ሃሳብ ከዘፍጥረት አንድ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን። በዚህ ምዕራፍ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ የምናየው የፍጥረት ሥራ የተሰራው በተናጠል ሳይሆን በሥላሴ ነው። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአንድነት በአንድ ሀሳብ ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት አብረው ፈጥረዋል። ዘፍጥረት 1፥1-3, 26፣ ዮሐንስ 1፥1-3

በአዲስ ኪዳንም ዮሐንስ 5፥9 ላይ ጌታ ራሱ ሲናገር « ... ወልድ በራሱ ምንም አያደርግም።» ይላል። ጌታ ያለአባቱ ብቻውን በተናጠል ምንም እንደማያደርግ ማስረዳቱ ነው። ሥላሴ የሚሰራው በተናጠል ሳይሆን በአንድነት ነው። ይህም ለቡድን ሥራ ጥሩ ምሳሌ ነው።

#### 2.1.1 የቡድን ተጫዋቾች

ሀ) አዳምና ሄዋን
ለ) አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች (የእግዚአብሔር ሕዝብ)
ሐ) ሙሴና አሮን
መ) ዳዊትና ወታደሮቹ
ሰ) ነህምያና የቀሩት የእግዚአብሔር ግንበኞች
ረ) ጳውሎስና በርናባስ
ሰ) ጳውሎስና ጢሞቴዎስ
ሸ) የቢሊግራም የወንጌል ዘመቻ ቡድን
ቀ) ወዘተረፈ

### 2.2 የክርስቶስ ምሳሌነት

ክርስቶስ ያለማንም እርዳታ ብዙ አስደናቂ ታምራት አድርጓል። እውር አብርቷል፤ አንካሳ አዘልሏል፤ የሞተ አስነስቷል፤ የባህሩን ማዕበል ጸጥ አድርል። አምላክ በመሆኑ የሰዎች እርዳታ ያላስፈለገው ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ የላከውን ሥራ ለመፈጸም አብረውት የሚሰሩ (ሰዎች) መርጧል።

ሀ) 3 አባላት (ማቴዎስ 26፥37)
ለ) 12 አባላት (ማቴዎስ 10፥1-5)
ሐ) 70 አባላት (ሉቃስ 10)
መ) ሰባዎቹን ለአገልግሎት ሲሰድ ለየብቻ ሳይሆን ሁለት ሁለት አድርጐ (በቡድን ) ሰደዳቸው። ( ሉቃስ 10፥1 )

## 2.3. የአዲስ ኪዳን ሞዴል

በአዲስ ኪዳን የቤተክርስቲያንን ምንነት የሚገልጹ ብዙ ሥዕላዊ ቃላት አሉ። ከእዚህ ውስጥ የቤተክርስቲያንን ምንነት በበለጠ የሚገልጸው አካል (body) የሚለው ቃል ነው።

| | |
|---|---|
| ኤፌሶን 1፥22-23 | ቆላስይስ 1፥18 |
| ኤፌሶን 4፥12-16 | 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥12-27 |
| ኤፌሶን 5፥23 | ሮሜ 12፥4-8 |

## 2.4 አካላዊ አገልግሎት

ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ «አካል» የሚለውን ቃል በሚከተሉት መንገዶች ተጠቅሞበታል።

ሀ) በጥሬ ቃሉ (ሰውነትን ለመጥቀስ)
ለ) የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያንን ለመጥቀስ
ሐ) የቤተክርስቲያንን አገልግሎት ለመጥቀስ



አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉት ቤተክርስቲያንም በክርስቶስ ዳግም በተወለዱ ግለሰቦች የተገነባች ነች። እያንዳንዱ አማኝ በአካሉ ውስጥ ቦታ አለው። የአካል ብልቶች በኅብረትና በአንድነት አንዱን አካል ለመጥቀም እንደሚሰሩ የአማኞችም አገልግሎት አካላዊ አገልግሎት ነው።

በአማኞችም መካከል አንዱ ከሌላው የሚለይበት ብዙ መንገድ አለ።

- በተፈጥሮ ችሎታ
- በቀሰምነው እውቀትና በሰለጠንበት ሙያ
- ከመንፈስ ቅዱስ በተቀበልነው የጸጋ ስጦታዎች (ሮሜ 12፥6፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥21)

የቤተክርስቲያን አንድነት ልዩ ልዩ መሆንን አይደመስስም። እያንዳንዱ እየተጨፈለቀ ከሌላው ሰው ጋር ተመሳሳይ እንዲሆኑ አይደረግም። ያ ቢሆን አንዱ የሌላው ኮፒ ብቻ ይሆናል። በአገልግሎት ቡድናችን ሆነ በቤተክርስቲያን ያለን አንድነት ልዩ ልዩ መሆንን የሚደመሰስ አይደለም። ቁጥራቸው 12 ብቻ በነበረው የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ( ቡድን ) ውስጥ እንኳን ብዙ ልዩነቶች ይታዩ ነበር።

| | |
|---|---|
| የሥራ | አሳ አጥማጆች፣ ገበሬዎችና ቀረጥ ሰብሳቢዎች ነበሩ። |
| የአመራር ችሎታ | መሪዎችም ተከታዮችም ነበሩበት።<br>ጴጥሮስ ቀደም ቀደም ባይ፤ መብቱን አስጠባቂ<br>ባህርይ ያዕቆብ እሳተ ገሞራ<br>ናትናኤል ገራም<br>ጴጥሮስ የደርጊት ሰው<br>ዮሐንስ የጸሎት ሰው<br>እንድርያስ የማይሽቀዳደም |
| አቀራረብ | ፊሊጶስ ከመናገሩ በፊት የሚያስብ -<br>ጴጥሮስ ከማሰቡ ቀድሞ የሚናገር |
| የፖለቲካ አመለካከት | ማቴዎስ የሮም መንግስት ታክስ ሰብሳቢ(ባንዳ)<br>ሰምዖን (ቀንአናዊው) በሮም ላይ የሚያምጽ አብዮተኛ |

ይህና ሌሎችም ልዩነት ሁሉ በቡድን ውስጥ ለቡድኑ ተመሳሳይ ውጤት ለማምጣት በአንድ ዓላማ ከማገልገል አላገዳቸውም።

ብልቶች መስራት የሚችሉት በተናጠል ሳይሆን በአንድ ላይ እንደሆነ በቤተክርስቲያንም ማገልገል የሚቻለው በተናጠል ሳይሆን በአንድ ላይ (በቡድን) ነው። የተሰጡንም የጸጋ ስጦታዎች የሚሰሩት በአንድ ላይ ነው። አንድ ሰው «ለብቻዬ አገለግላለሁ» ብሎ ቢነሳ ከንቱ ድካም ከማድረጉም በላይ የመጽሐፍ ቅዱስን ሀሳብ ይቃወማል።

ምሳሌ ሀ) በሁለተኛው ዓለም ጦርነት አንዱ የቀኝ እጁን ሌላው የግራውን ያጡ ጓደኞች። በአንድ ትእይንት ቦታ ለብቻቸው ማጨብጨብ ስለማይችሉ ጐን ለጐን ሆነው በአንድ ላይ ማጨብጨባቸው።

ለ) እውሩና ሽባው። እውሩ መራመድ ይችላል ማየት አይችልም። ሽባው ደግሞ ማየት ይችላል መራመድ አይችልም። ሁለቱ ግን በአንድ ላይ ሆነው የጎደላቸውን ያሟላሉ።

የቡድን አገልግሎት የታወቀትን የአገልጋዮች በሽታ (ውድድር፣ ቅናት፣ ግጭት) አስወግዶ ትብብርንና መረዳዳትን ይፈጥራል። የአንዱ ጉድለት በሌላው ይሸፈናል። ለዚህ ነው ቤተክርስቲያን የቡድን ስራን ማደፋፈርና ማዳበር ያለባት። አማኞችም እን ደስጦታቸው በቡድን ተሰልፈው አስተዋጽዖ ማድረግ አለባቸው። የእግዚአብሔርን ሥራ እኔ እገሌ አሉ በማለት ችላ ማለት ትልቅ ስህተት ነው።

ምሳሌ - የሦስቱ ወንድማማቾች ድግስ
ሁሉም እኩል ሊያዋጡ በተስማሙበት ድግስ እያንዳንዳቸው ሌሎቹ የሚያመጡት ይበቃል ብለው ለየብቻ በማሰባቸውና ውሃ በማምጣታቸው ድግሳቸውን አበላሹ።



# 3. የቡድን ሥራ ጥቅምና አስፈላጊነት

## 3.1. በቡድን የመስራት ውጤት

### 3.1.1. ብዙ ውጤት ይኖራዋል (Synergy)

በቡድን ውስጥ ብዙ ጉልበት፣ ብዙ ችሎታ አለ። ስለሆነም በተናጠል ሰርተን ከምናፈራው ይልቅ የበለጠ ፍሬያማ መሆን ይቻላል።

### 3.1.2. እያንዳንዱ በታጠቀበት ይሠራል

በቡድን ስንሠራ የሥራ ክፍፍል ስላለ ሁሉም በታጠቀበት (በችሎታና ስጦታው) መሥራት ይችላል።
በኤፌሶን - 4፥15-16 ሐዋርያው ጳውሎስ የሚነግረን እያንዳንዱ አማኝ (ብልት) የታጠቀበትን አገልግሎት እንዲያገለግል ነው። ፍሬያማ መሆን የምንችለው በታጠቅንበት ስጦታና ችሎታ ለመሥራት ስንሰለፍ ነው።

ምሳሌ - የእንስሳት ት/ቤት
- የኮርሱ ዓይነት - በረራ፣ ሩጫ፣ ዋና
- ተማሪዎቹ - ጥንቸል፣ ንስር፣ ዳክዬ
- ጥንቸል ጎበዝ የሆነችበትን ሩጫን ትታ በበረራ ስለተመዘገበች በመሰባበርዋ ያመጣችው ወጤት ይህ ሆነ።ጎበዝ በነበረችበትም ሩጫ ደካማ ሆነች።
- ዳክዬ ዋናን ትታ በሩጫ በመመዝገብዋ ወላልቃ ዋናውም ሳይቀር የማይሆንላት ሆነ።
- ንስር ብርታትዋ የነበረውን መብረር ትታ በዋና ስለተመዘገበች ክንፍዋ በውሃ ተበጣጥሶ ከዚያ ወዲህ መብረርም የሚሳናት ሆነች።

ባልታጠቅንበት (ያለስጦታችን) የመሰለፍ ውጤት በእነዚህ እንስሳዎች ላይ የደረሰው ዓይነት ውጤት ከማምጣቱም በላይ የቡድንን ስራ ይጎዳል። በታጠቅንበት ለመሥራት ብልትንና ብልትን የሚያያይዙት መጋጠሚያዎች በደንብ መሥራት አስፈላጊ ነው። መጋጠሚያዎች በትክክሉ ሳይጋጠሙ ሲቀር ውልቃት ይኖራል፤ ሕመም ይሰማል። በቡድን ሥራ መጋጠሚያዎች ( ኅብረት - fellowship ) በጣም አስፈላጊ ናቸው።

### 3.1.3. የእግዚአብሔር እቅድና ፕላን

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን የሚመለከታት እንደ አንደ አካል ነው። ለእርሷም ያለው እቅድ ብልቶች እርስ በእርስ በትክክል እየተጋጠሙ አካሉን እንዲያሳድጉ ነው። በአንድነትና በቡድን መስራት በሥላሴ አሰራር ውስጥ የሚታይ እንደሆነ ቀደም ሲል ጠቅሰናል። ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ ያለአባቱ በተናጠል ምንም

እንደማያደርግ ተናግሮአል። (ዮሐንስ 5፥9) የእግዚአብሔርን ሃሳብና ዓላማ የተከተሉ ሥራዎችም ውጤት የሚኖራቸው ከኅብረትና ከአንድነት ነው። ሰለሞን እንደሚለው ይህንን የእግዚአብሔር ሃሳብ የማይከተል መልካሙን ጥበብ ይቃወማል። ( ምሳሌ 18፥1 )

### 3.1.4 የጸጋ ስጦታዎች እንዲሰሩ የታቀደው በአካል ውስጥ ነው

መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለእያንዳንዱ ስጦታ የሚሰጠው እያንዳንዱ ለአካሉ ግንባታ ሥራ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቁጥራቸው ከ25 በላይ የሚሆኑ ስጦታዎች መኖራቸውን ያስተምረናል። (1ኛ ቆሮንቶስ 12፥8-10,
1ኛ ቆሮንቶስ 12፥28፤ ሮሜ 12፥6-8፤ ኤፌሶን 4፥11ና 1ኛ ቆሮንቶስ 13 )

ሀ) እንዚህ ሁሉ ስጦታዎች የሚሰጡት ለግል እርካታ ሳይሆን ለአካሉ (ቤተ ክርስቲያን) መገንባትና መታነጽ ነው።
ለ) መገንባትና መታነጽ ወደላይና ወደጐን (ብዛትና ጥራት) ያለውን የዕድገት አቅጣጫ ይመለከታል።

« የአንድ ቡድን አባላት በሙሉ በአንድ ላይ መጫወት ለቡዱኑ ስኬታማነት ወሳኝ ነው። በዓለም ዝነኛና ታዋቂ ስፖርተኞችን ብንሰበስብ በቡድን ካልተጫወቱ ያ ቡድን የ 10 ሳንቲም ያህል ዋጋ አያወጣም።»
(New York Yankees )



### 3.1.5 በቡድን መሥራት የዳበረ የችሎታና የኃይል ምንጭ (resource) ይሰጣል

ቡድን ብዙ የተለያየ ሪሶውርስ ይሰጣል፥
ሀ) የተለያየ ስጦታና ችሎታ ይገኛል
ለ) ልዩ ልዩ ሰዎች (Personalities) ይሰጣል። (ይህ ለሥራ አመዳደብና አከፋፈል ይረዳል።)
ሐ) ብርታት ይሰጣል
መ) ልዩ ልዩ ልምምድ (experience) ይኖራል።

### 3.1.6 በቡድን መሥራት የዳበረ የሃሳብ ባንክ ይሰጣል

የተለያየ ጠቃሚ ሃሳብ ስለሚሰበሰብ ለትክክለኛ ውሳኔ ይረዳል። የማይፈለጉት ሃሳቦች በስራ ላይ እንዳይውሉ ይቆጣጠራል። (check & balance)

### 3.1.7 ተጠያቂነትን ( accountability) ይመሰርታል

በአጠቃላይ ለቡድኑና ለግለሰቦችም የተጠያቂነት ስሜት ስለሚያሰማ በስራ (አገልግሎት) ትጉ ያደርጋል።

### 3.1.8 ውጤቱ (ፍሬው) ይበዛል

አንድ ፈረስ ለብቻው 2,000 ኪሎ ቢጎትት ሁለት ፈረሶች በቡድን 23,000 ኪሎ መጐተት ይችላሉ።
አንድ ሰው ለብቻው 1,000 ያባርራል፤ ሁለት ሰዎች በቡድን 10,000 ያባርራሉ። ዘዳግም 32፥30
የሁለት ሰዎች ውጤት ቢደመር 2,000 ብቻ ይሆን ነበር። በመባዛቱ ግን የ8,000 ተጨማሪ ውጤት ተገኘ።

ምሳሌ 11፥14 መክብብ 4፥9-13 ምሳሌ 15፥22 ምሳሌ 24፥6

### 3.1.9 አርስ በእርስ መሳሳል ይቻላል

« ብረት ብረትን ይስለዋል፤ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል።» ምሳሌ 27፥17።
አዲሱን በሬ ከአሮጌው በሬ ማቀናጀት አዲሱ እንዲሰለጥን ይረዳዋል።

## 3.1.10 እርስ በእርስ ለመጠባበቅ ያስችላል።

ወታደሮች በቡድን ሲዋጉ አንዱ ወገን ስትራቴጂካዊ ቦታ እንዲይዝ ወደፊት ሲቀድም ሌላው ሽፋና ይሰጣል። 1ኛ ዜና መዋዕል 19፥6-16 ላይ የዳዊት ጦር በአሞናውያንና በቅጥረኞቹ ሶርያውያን ወታደሮች መካከል እንደ ሳንድዊች በሆኑ ጊ ዜ ኢዮአብ ጦሩን ለሁለት ከፍሎ ጀርባ ለጀርባ ሆነው መዋጋታቸው እያንዳንዳቸው የችግሩን ግማሽእንዲያቃልሉና ሁለቱንም የጦር ግንባር በመሸፈን ከጉዳት እንዲጠ ባበቁ ረድቷል።

ምሳሌ ጅብና በቅሎዎች

በቅሎዎች ራስ ለራስ ገጥመው ሁሉም የኋላ እግራቸውን በመወርወር ጅብን መከላከል ቻሉ። ቀደም ብሎ ግን እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ለማዳን ሲዘሉና ሲራገጡ ጅብን ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ተጎዳድተው ነበር።

## 3.1.11 በቡድን መስራት አካሉን ቶሎ ይገነባል

ለብቻ ከሚሠራ ሥራ ይልቅ በቡድን የሚሠራ ሥራ ቶሎ ፍጻሜ ያገኛል።

- ጅጌ
- ደቦ
- የቢስ ኩባንያ ዕቃ ጫኞች

በቡድን መስራት መነቃቃት ይሰጣል። ( ዕብራውያን 10፥24 ) (group incentives) አለበት።



## 3.1.12 የሥራ ቅደም ተከተል (priority) ለማስተካከል ይረዳል

የሐዋርያት ሥራ 6፥2-7

## 3.1.13 ትልቁ ሥዕል ላይ ለማተኮር ያስችላል

ሰዎች ትልቁን ነገር ማየት ትተው በትንሹ ላይ በማተኮር ከግባቸው እንዳይወሰዱ ይረዳል።

ምሳሌ የወደቀውን ትልቅ ዳቦ ባለማየት በፍርፋሪው ምክንያት ይጨናቆሩ የነበሩት ወፎች። በእንግሊዝኛ " An ounce of prevention is worth a pound of cure " ይላሉ። በቡድን ልንሠራ ስንነሳ የሥራችን ውጤት እንዳይጎዳ አስቀድመን ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሁሉ መውሰድ አስፈላጊ ነው።

## 3.2. ማጠቃለያ

« ለሌላው ያካፈሉት ደስታ እጥፍ ደስታ ያካፈሉት ሃዘንም ግማሽ ሃዘን ነው።» የስዊድኖች ምሳሌያዊ አነጋገር።

### 3.2.1. አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል

መክብብ 4፥9-12

ሀ) መሰረታዊ መመሪያ

«አንድ ከመሆን ሁለት ... » (ቁጥር 9)፣ ዘፍጥረት 2፥18

ለ) ሁለት መሆን አንድ ከመሆን የሚሻልበት ምክንያት

1) የሌላው እርዳታ ስለሚያስፈልግ

«አንደኛው ቢወድቅ ሁለተኛው ያነሳዋል።» (ቁጥር 10)

2) ብቸኛ ለችግር የተጋለጠ ስለሆነ።

«አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።» (ቁጥር 12)

### 3.3.2 የሙሴ አማች የዮቶር ምክር (ዘጸአት 18፥1-27)

የሥራ ማከፋፈል (delegation) ሲኖር አካሉ የቡድን ሥራ ከአመጣው በረከት ተካፋይ ይሆናል። ግለሰቦችም ከሚገባው በላይ በመሸከም አይጎዱም።

> «የሺ ሰዎችን ሥራ ከመሥራት ሥራን ለሺ ሰው ማካፈል ይመረጣል።»
> ዲ. ኤል. ሙዲ
>
> የሐዋርያት ሥራ 6፥1-7 ላይ ሐዋርያት ያደረጉት ውሳኔ ውጤት ቤተክርስቲያን እንድታድግ አድርጓል። (የሐዋርያት ሥራ 6፥7)
>
> የቡድን ስራ ለሥራው ሆነ ለግለሰቡ ጠቃሚ ነው።
> «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር።»

## 4. የቡድን ሥራ እንዲቀላጠፍ የሚረዱ ነገሮች

የቡድን ስራ የተቀላጠፈ ሆኖ ውጤት እንዲኖረው የሚያደርጉ ብዙ ነገሮችአሉ። እነርሱም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው።

### 4.1 መሰጠት (commitment)



መሰጠት ሳይኖር ስኬት የሚገኝበት ምንም ነገር የለም። ሁሉ ነገር መሰጠትን ይጠይቃል።

> ዲ. ኤል. ሙዲ ለወንጌል አገልግሎት የተሰጡትና ፍሬ ያፈሩት አንድ ሰባኪ «እስከ ዛሬ ድረስ ዓላማችን ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሰው ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ገና አላየችም።» ብሎ ሲናገር ስምተው ያንን ሰው ለመሆን ወሰነው እንደሆነ ይነገራል።

እግዚአብሔር የተሰጠ ሰው ይፈልጋል የተሰጠ ሰው ካለ ያ ሰው የሚጐድለውን ሁሉ እግዚአብሔር አሟልቶ በዚያ ሰው ታሪክ መሥራት ይችላል። ራስን አለመስጠት ራስን ለእግዚአብሔር አገልግሎት አለማቅረብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ራሳቸውን ላለማቅረብ ምክንያት ያበዙ ሰዎች እንዳሉ እናያለን።

#### 4.1.1 ኤርምያስ - (ኤርምያስ 1፥4-8)

> ራሱን ላለመስጠት «ልጅ ነኝ።» የሚል ምክንያት አቀረበ።

#### 4.1.2 ሙሴ - (ዘጸአት 3፥ 7-10፣ ዘጸአት 4፥1-13)

ሙሴ ለእግዚአብሔር ብዙ ምክንያት አቅርቧል። እውነቱ ግን ዘጸ.4፥13 ላይ እንደ-ተ ጻፈው ራሱን ለመስጠት አለመፈለጉ ነበር። እግዚአብሔር መሰጠታችን ይያዝ እንጂ ጉድለታችንን መሸፈን (ማሟላት) አያቅተውም። አለም በወንጌል መገለባበጥ የምትችለውና በቡድን የሚሰሩ የእግዚአብሔር ሥራዎች ሁሉ ፍሬያማ የሚሆኑት በተሰጡ ሰዎች መገኘት ነው።

### 4.2 መቀባበል

አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት እርስ በእርስ እንዲቀባበሉ ማሰልጠን አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም 12 የተለያዩ ሰዎች እንደሆናቸው መጠን በመካከላቸው ብዙ ልዩነቶች ነበሩ።

- በቡድኑ ወንድማማቾች ነበሩ።
- እንድርያስና ዮሐንስ የመጥምቁ ተከታዮች ስለነበሩ በልምምድ ብልጫ ታብየው ጀማሪዎች በሆኑት ሌሎቹ ላይ መኩራራት ይችላሉ።
- ቀንአናዊው ስምኦንና ቀራጩ ማቴዎስ ከተለያየ የኑሮና ፖለቲካ ልምምድ ስለሚመጡ ትልቅ ችግር መፈጠር ይችል ነበር።

ልዩነት መቀባበል እስካለ ድረስ አንድን ቡድን ይጠቅማል እንጂ አይጐዳም። የጥንት ክርስቲያኖችን ስንመለከት ብዙ ልዩነት እንዳላቸው እናያለን። እንደ ማቴዎስ አይሁዳዊ፣ እንደ ቆርኔሌዎስ አሕዛብ፣ አንደ ጢሞቴዎስ የሁለቱ ዘር ቅይጥ (ክልስ)፣ እንደ አጵሎስ የተማሩ፣ አንደነ ጴጥሮስና ዮሐንስ ያልተማሩ፣ እንደ ጳውሎስ ጽኑ የሆነ በእምነት የዳበረ አስተዳደግ፣ እንደ ቆሮንቶሳውያን ጣዖታዊ ልምምድ፤ እንደ ጴጥሮስ ችኩሎች፤ እንደ በርናባስ ትዕግስተኞችና ልበ ሰፊዎች፤ እንደ ሉቃስ አስተዋይና አዋቂ እንደ ፊልሞና ነጻ የነበሩ፤ አንደ አናሲሞስም ባሪያዎች ነበሩባቸው። ልዩነታቸው ብዙ ቢሆንም ኅብረታቸውን ወይም የቡድን አገልግሎታቸውን አልነካውም። የድል ምስጢራቸው መቀባበል ነበር። መቀባበል ለቡድን ሥራ ስኬት አስፈላጊ ነው። ( ሮሜ 15፥6 )

## 4.3 ተስማምቶ መሥራት

በቡድን ውስጥ የተለያየ ሃሳብ መኖር ቡድኑን ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም። ሥራው የሚሠራው ግን የመስማማትን መመሪያ በመከተል ነው። ቡድን የችሎታና የኃይል ግምጃ ቤት ነው። የተለያየ ቾሎታ ያላቸው ሰዎች አብሮ ለመስራት የግድ የመስማማትን መመሪያ መከተል ያስፈልጋል።



### 4.3.1 ነገር ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ይጸናል

ማቴዎስ 18፥16 የመስማማትን መመሪያ የተከተለ ነው። የአንድ ሰው ቃል ሚዛን የሚኖረው ሌላው ሲስማማ ብቻ ነው።

### 4.3.2 የቡድን ጸሎት መልስ መስማማት ላይ የሚመካ ነው

ማቴዎስ 18፥19

### 4.3.3 የስፖርት ውድድር

የቡድን አገልግሎት የመስማማትን መመሪያ እንደሚከተል ለማወቅ እንደ ስፖርት ጨዋታ የሚረዳ ምሳሌ የለም።

ሀ) የጀልባ ውድድር
- አንድ አቅጣጫ (ወደተለያየ አቅጣጫ ቢቀዝፉ ጀልባዋ ትሽከረከራች)
- የቡድን ጥረት
- የግል ትእይንት ጎጂ ነው። ምሳሌ፥ አብዶ በመፍጠር ታላቅ አድናቆት የሚያመጡ ቡድናቸው ግን የሚሸነፍ ተጫዋቾች አሉ።

ለ) ባስኬትቦል
- ሀኪም አላጃዋን ታላቅ ዋጋ ያለው ተጫዋች (MVP) ተብሎ ሲሸለም የተናገረው፥ «ይህ ሽልማት የኔ ጥረት ውጤት ሳይሆን የቡድኑ ነው።» ማለቱ የሚዘነጋ አይደለም።
- ፓትሪክ. ኢዊንግ ያለው......

## 4.4 መተማመን (trust)

በቡድን አባላት መካከል መተማመን መኖሩ ለቡድኑ ስኬት ጠቃሚ ነው።

## 4.5 ግልጽነት (openness)

ሁሉን ነገር በግልጽ ለመነጋገር መቻል ለቡድኑ ስኬት ይጠቅማል።

## 4.6 ፍቅር

ከዚህ በፊት በተመለከትነው ኤፌሶን 4፥15-16 ላይ ስለፍቅር ጠቃሚ ነገር እናያለን። ብሎቶች እርስ በእርስ በትክክሉ እንዲገጣጠሙ የሚያደርገው ማጣበቂያ ሙጫው ፍቅር ነው።

4.7 ጥሩ የሀሳብ ልውውጥ (good communication)

## 5. የቡድን አገልግሎት ሊያጋጥሙት የሚችሉ መሰናክሎች

### 5.1. ስለሹመት ስም (title) የተሳሳተ አመለካከት መያዝ

- ዲያቆን
- ዘማሪ
- የመዘምራን መሪ
- የሙዚቃ ድሬክተር
- ወዘተ. . . . .

እነዚህ ሁሉ ከአቻዎች መካከል ለስራው ስለተመረጡ እንጂ ያለእነርሱ ለሥራው ችሎታ ያለው ሌላ ሰው በቡድኑ መካከል የለም ማለት አይደለም።

- አገልጋዮች ዝቅ ብሎ ማገልገልን (servant leadership) ዓላማቸው ሊያደርጉ ይገባቸዋል። ዮሐንስ. 13፥14-16 ማቴዎስ 20፥27-28።

### 5.2 ቅናትና ትዕቢት



ጤነኛ ያልሆነ ውድድር ካለ ቅናት ይፈጠራል። ቅናት ከአገልጋዮች በሽታ ውስጥ ኃይለኛውና ጐጂው ነው።

- የሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱ ያለው አመለካከት (attitude)

ሀ) «ሎሌዎች ነን።» 1ኛ ቆሮንቶስ 4፥1,2
ለ) «የሚተክል ሆነ የሚያጠጣ አንዳች አይደለም።»
1ኛ ቆሮንቶስ 3፥7 አንዳች ያልሆነን 0 ( ዜሮ ) ብለን በናስብ 0 ከ 1 ቁጥር ቢፊት ሲሆን የአንድን ዋጋ ያሳንሳል 0 የ 1 ቁጥርን ዋጋ የሚጨምረው ከ 1 በኋላ ሲደረደር ብቻ ነው።

### 5.3 ግልጽ ያለመሆን

ግልጽነት የሚጠቅመውን ያህል ግልጽ ያለመሆን ደግሞ ለቡድን ሥራ ጐጂ ነው።

### 5.4 የሀሳብ ልውውጥ ጉድለት (failure to communicate)

### 5.5 በሌላው ቦታ ራስን አለማስቀመጥ

« በሌላው ጫማ ከመቆምህ በፊት አትፍረድ »

## 6. የቡድን መንፈስ (Team spirit)

« አብሮ መሰብሰቡ ጅማሬ ነው። አብሮ መቆየቱ እድገት (progress) ነው። አብሮ መስራት ስኬት ነው።» ሄንሪ ፎርድ

ከዚህ በፊት የቡድን መንፈስ ማለት እያንዳንዱ ሰው እንደቡድን አባልነቱ ለመተባበር የሚያሳየው ፈቃደኝነት እንደሆነ ተነጋግረናል።

- የአንድ ቡድን ወይም የአገልግሎት ዘርፍ መቋቋሙ ጅማሬ ነው። ቡድኑ አብሮ መቆየቱም እድገት ነው። ምክንያቱም ብዙ ነገሮች እየተጀመሩ ቶሎ ደግሞ ይፈርሳሉ። ነገር ግን የአንድ ቡድን አብሮ መቆየትም ቡድን የተቋቋመበትን ዓላማ እየፈጸመ ለመሆኑ ምስክር አይደለም። ብዙ በሥም ብቻ በቡድንነት ያሉ የሚመስሉ፣ ውስጣቸው ግን ብዙ ችግር ያለባቸው አሉ። አብሮ መሥራት ካልተቻለ የቡድን መኖር በራሱ ስኬት የለውም።

- ዛሬ በቡድን ለሚሰሩ ስራዎች ሰራተኛ የሚመለምሉ ድርጅቶች በምልመላው

ሰዓት ሰውዬውን ከሚመዝኑበት መንገድ አንዱ የቡድንን መንፈስ የሚጠብቅና የማይጠብቅ መሆኑን ነው። የራሱን ግብ በቡድን ግብ ተክቶ በኅብረት ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ለቡድን ሥራ አይጠቅምም። በቤተክርስቲያን አገልግሎትም የቡድን መንፈስ መጠበቅ ያለበት ነገር ነው።

## 6.1 የቡድን መንፈስ የሚያካትታቸው ነገሮች

ምንም እንኳን የቡድን መንፈስ የሚያካትታቸውን አብዛኛዎቹን ነገሮች በሌላ ርእስ ስር የተመለከትናቸው ቢሆንም የሚጠቅሙ በመሆናቸው በድጋሚ እንመለከታቸዋለን።

### 6.1.1 **መከባበር** (mutual respect)

መከባበር ከሌለ አብሮ መሥራት ይከብዳል።

### 6.1.2 **መቀራረብ** (closeness)

ካልተቀራረቡ መፈራራት ይኖራል። መፈራራት አብሮ የመሥራት ፈቃደኝነትን ይገድላል።

### 6.1.3 **መተማመን** (trust)



### 6.1.4 **መቀባበል** (acceptance)

### 6.1.5 **ማበረታታት** (encouragement )

### 6.1.6 **ጥሩ የሃሳብ ልውውጥ** (good communication)

# 7. የቡድን መሪ

ሁሉ ነገር መሪ ያስፈልገዋል። ድርጅቶች ቤተክርስቲያን፣ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሁሉ መሪ ያስፈልጋቸዋል። ያለመሪ የቡድን ሥራ አይሠራም። መጽሐፍ ቅዱስ የቡድንን ሥራ (አካላዊ አገልግሎት) ቢያስተምርም የመሪን አስፈላጊነት ደግሞ ከሥላሴ ምሳሌነት ጀምሮ ያስተምራል።

- አብ - የሥሳሴ ራስ ነው
- አብ የክርስቶስ ራስ ነው
- ባል የሚስት ራስ ነው
- እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን አመራርን አድርጓል

«ምዕመን ሁሉ መሪ አገልጋይ ሁሉ ምዕመን» የሚለው ሀሳብ የሚሠራበትና የሚጠቅምበት መንገድ አለ። የመሪን አስፈላጊነት ግን አይደመስስም።

- ያለመሪ የቡድን ሥራ ግብ አይመታም። አይሠራምም።

## 7.1 መሪ የቡድን አባላትን መምረጥ ማደራጀት መምራት አለበት

### 7.1.1 መቋቋም ባለበት ቡድን ውስጥ ያለውን ስራ መዘርዘር

### 7.1.2 ለቡድኑ የስራ ዝርዝር (job description) መሥራት

### 7.1.3 ለሥራው ተገቢ የሆኑትን ሰዎች ዝርዝር ማውጣት

### 7.1.4 ለሥራው የታጩትን ሰዎች እያንዳንዱን በግል ማናገር

### 7.1.5 ለመሥራት ፈቃደኞች የሆኑትን ተከታትሎ ሥራውን ማስጀመር

ይህ ሁሉ በሚደረግበት ጊዜ ( ለቤተክርስቲያኑ አገልግሎት )

- ጥሩ የሕይወት ምስክርነት
- ለቤተክርስቲያንና ለቡድኑ ዓላማ ታማኝነት
- ለአገልግሎቱ ሸክም እንዳላቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው።

